## 2ኛ ቀን

### አንብቦ መረዳት

**ጥያቄዎቹን በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።**

1. እነሰይድ ያጠፉት ጥፋት ምንድን ነው?
2. እናንተ እነሰይድን ብትሆኑ ምን ታደርጉ ነበር?

### ቃላት

**በምሳሌዎቹ መሠረት ዓረፍተነገር ፃፉ።**

ምሳሌ፦ እርሳስ → እርሳሴ ጠፋ።

እርሳሶች → እርሳሶቼ ጠፉ።

1. መርፌ
   መርፌዎች
2. ክፍል
   ክፍሎች
3. ግቢ
   ግቢዎች

### መፃፍ

**ድርጊቶችን በቅደምተከተል ፃፉ።**

| 1 | 2 |
|---|---|
| • ቆሻሻን ማቃጠል<br>• ግቢን መጥረግ<br>• ቆሻሻን ጉድጓድ ውስጥ መጨመር | • እጅን በሳሙናና በውሃ መታጠብ<br>• ወደመፀዳጃ ቤት መሄድ<br>• የመፀዳጃ ቤትን ጉድጓድ አፍ መክደን<br>• በመፀዳጃ ቤት ጉድጓድ አፍ ላይ በትክክል መፀዳዳት |

ምሳሌ፦ 1. በመጀመሪያ → ግቢን መጥረግ

ከዚያ በኋላ → ቆሻሻን ጉድጓድ ውስጥ መጨመር

በመጨረሻ → ቆሻሻን ማቃጠል

## 3ኛ ቀን

## ማዳመጥ

### ንፅህና ለጤና

## ቃላት

ስለታም የሆኑና ያልሆኑ ነገሮችን ዘርዝሩ።

| ስለታም የሆኑ | ስለታም ያልሆኑ |
|---|---|
| ምላጭ | ፎጣ |

## ማጣመር

ተስማሚ ፊደላትን በመምረጥ ቃላትን በቃላችሁ መስርቱ።

| ሰ | ደ | ከ | ሀ | |
|---|---|---|---|---|
| ብ | ል | ር | ያ | ምሳሌ፡- ጥፍር |
| ገ | ት | ማ | ቀ | |
| ነ | ጅ | ጥ | ፍ | |

## ግለንባብ

### በጤንነት ለመኖር




በጤንነት ለመኖር ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው። በቅድሚያ የግልን ንፅህና መጠበቅ ያስፈልጋል። ከሌሎች ሰዎች ጋር በጋራ የማንጠቀምባቸው የንፅህና መጠበቂያ መሣሪያዎችን ማወቅ የግድ ነው። እንደምላጭ፣ መርፌና ሌሎች ስለታም ነገሮችን እንዲሁም የጥርስ ቡርሽና ፎጣዎችን በጋራ መጠቀም የለብንም። ምክንያቱም ለኤች አይ ቪ ኤድስና ለሌሎች ተላላፊ በሽታዎች ያጋልጡናል።

# 4ኛ ቀን

## አንብቦ መረዳት

**ጥያቄዎችን በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።**

1. ኤች አይቪ ኤድስ ሲባል ሰምታችሁ ታውቃላችሁ?
2. ኤድስ እንዳይዘን ምን ማድረግ ይኖርብናል?
3. ከሌሎች ሰዎች ጋር በጋራ የማንጠቀምባቸውን ዕቃዎች ዘርዝሩ።

## ቃላት

**ዓረፍተነገር ፃፉ።**

ምሳሌ፦ ወጋች → ዓለሚቱ እጇን በመርፌ ወጋች።

1. ቆረጠች
2. ጠረገች
3. ፋቀች

## መፃፍ


**ሥርዓተነጥቦችን በትክክል በመጠቀም መምህራችሁ የሚነግሯችሁን ዓረፍተነገሮች አዳምጣችሁ ፃፉ።**

## 14ኛ ሳምንት

### 1ኛ ቀን

### ማዳመጥ

የተመጣጠኑ ምግቦችና አስፈላጊነታቸው




### ቃላት

በቃላችሁ ዓረፍተነገር ሥሩ::

1. ዓሳ
2. አተር
3. ወተት
4. ሎሚ

### ማጣመር

ፊደላቱን በክፍት ቦታዎች በመፃፍ ቃላትን መስርቱ::

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ጠ | ደ | ወ | ሰ | ጀ | ፈ | ጨ | ል | ሌ | ጅ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሰለቀ → ሰለቀ | ጀመረ → ጀመረ | ደረሰ → ደረሰ | ጅማት → ጅማት |
| _ለቀ → ____ | _ መረ → ____ | _ረሰ → _____ | _ ማት → ____ |
| _ለቀ → ____ | _ መረ → ____ | _ረሰ → _____ | _ ማት → ____ |

# ግለንባብ

## “ወይ አለማወቅ!”



“ተረኛ፣ ተረኛ!” አለ ነርሱ:: ወይዘሮ ታሪኳ፣ “አቤት!” ብለው የሁለት ዓመት ልጃቸውን ይዘው ገቡ:: “ምኑን ነው ያመመው?” ዶክተሯ ጠየቁ:: “አያዩትም! ፀጉሩ ሳስቷል፤ ሆዱ ተነፍቷል፤ ድዱም ይደማል” አሉ ወይዘሮ ታሪኳ:: ዶክተሯም፣ “በጣም ያሳዝናል፤ እንደዚህ ያደረገው የተመጣጠነ ምግብ አለማግኘቱ ነው:: አሁንም ወተት፣ እንቁላል፣ ማር፣ አትክልትና ፍራፍሬ ይመግቡት፤ ቶሎ ይሻለዋል፤ ለአሁኑ ግን መድኃኒት አዝለታለሁ” በማለት አስረዷቸው:: ወይዘሮ ታሪኳም “ወይ አለማወቅ! ልጄን በምግብ እጥረት ገድዬው ነበር” በማለት አለቀሱ::

## 2ኛ ቀን

### አንብቦ መረዳት

**ጥያቄዎችን በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ::**

1. የተመጣጠኑ ምግቦችን አለመመገብ ምን ጉዳት ያደርሳል?
2. ዶክተሯ ወይዘሮ ታሪኳን ምን ብለው መከሯቸው?

### ቃላት

**በምሳሌው መሠረት ቃላትን መድቡ::**

| ገንቢ ምግቦች | ኃይልና ሙቀት ሰጪ ምግቦች | ከበሽታ ተከላካይ ምግቦች |
|---|---|---|
| ወተት | ማር | ጎመን |

## መፃፍ

የፊደላትን ቦታ በማቀያየር ወይም በመቀነስ ቃላትን መስርቱ::

ምሳሌ፦ አቀረበች → ቀረ፣ ቀረበ፣ ቀረች፣ ቀበረ፣ አቀረበ...






1. ተመጣጠነ    2. አስፈላጊነት    3. አረጋገጠ

## 3ኛ ቀን

## ማዳመጥ

የተመጣጠኑ ምግቦችና አስፈላጊነታቸው

ሥዕሎቹን ከመግለጫዎቻቸው ጋር አዛምዱ::

| "ሀ" | | "ለ" | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | ሃይልና ሙቀት ሰጭ ምግቦች | ሀ. |  |  |  |
| 2. | ከበሽታ ተከላካይ ምግቦች | ለ. |  |  |  |
| 3. | ገንቢ ምግቦች | ሐ. |  |  |  |

## ማጣመር

የፊደላቱን ቦታ በማቀያየር ቃላትን መስርቱ::


ምሳሌ፦ ብ ሃ ል ት → ብልሃት

1. ክ ሪ ብ ት    3. ክ ረ ስ ት

2. ድ ቀ ር ት    4. ጥ ረ ም ት    5. ው ቀ ድ ት

# ግለንባብ

## ጤናማ አመጋገብ



ጤናማ አመጋገብ ማለት ከየምግብ አይነቱ በተመጣጠነ መልኩ የተዘጋጀ ምግብ መመገብ ማለት ነው። የተመጣጠነ ምግብ ገንቢ፣ ሃይልና ሙቀት ሰጪና በሽታ ተከላካይ ናቸው። አንድ ሰው በየቀኑ ከነዚህ የምግብ አይነቶች ሊያገኝ ይገባዋል። በተጨማሪም በስለው የሚበሉ ምግቦችን በደንብ አብስሎ መመገብና በጥሬው የሚበሉትን ደግሞ አጥቦና ንፅህናቸውን ጠብቆ መመገብ ይኖርበታል።

## 4ኛ ቀን

### አንብቦ መረዳት

**ለጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልስ ስጡ።**

1. ጤናማ አመጋገብ ማለት ምን ማለት ነው?
2. በስለው የሚበሉ ምግቦችን በጥሬው ብንመገባቸው ምን እንሆናለን?
3. በጥሬው የሚበሉ ምግቦችን ለመመገብ መጀመሪያ ምን ማድረግ አለብን?

### ቃላት

**በምሳሌው መሠረት ቃላትን መድቡ።**

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ሥጋ | ወተት | እንቁላል | ሰላጣ | ማንጎ |
| ብርቱካን | ድንች | ሙዝ | ዓሳ | ትርንጎ |

| በስለው የሚበሉ | በጥሬው የሚበሉ |
|---|---|
| 1. ሥጋ | 1. ሙዝ |

### መፃፍ

**የጥያቄውን መልስ ፃፉ።**

እንቁላል ለመጥበስ ምን ምን ነገሮች ያስፈልጋሉ?

## 15ኛ ሳምንት

### 1ኛ ቀን

### ማዳመጥ



**የንፅህና ጉድለት ጠንቆች**

### ቃላት

ዓረፍተነገር ሥሩ::

1. አስም 2. ተስቦ 3. ተቅማጥ 4. ዓይነማዝ

### ማጣመር

ፊደላቱን በማጣመር ቃላትን መስርቱ::


ምሳሌ:- አሰረ

| | | |
|---|---|---|
| አ | ሰ | ረ |
| በ | ለ | ጠ |
| ደ | ለ | በ |

| | |
|---|---|
| 1. | 4. |
| 2. | 5. |
| 3. | 6. |

### ግለንባብ

**"በቁማችን ሞተናል!"**



"ኡፍ! ኡፍ ውይ! ውይ! ወይኔ! ራሴ!" እያሉ ያቃስታሉ- አቶ ገዛኸኝ:: ጎረቤታቸው አቶ ምንተስኖት፣ "ምን ሆነሃል? ያች አስም ተነሳችብህ እንዴ? ይገርማል! በገዛ እጃችን የበሽታ መራቢያ እንሁን?" አቶ ገዛኸኝ ጥርሳቸውን እያፋጩ፣ "እስቲ ተመልከት! በዙሪያችን ያለው የቆሻሻ ክምር! የቆሻሻው ሽታስ አፍንጫችንን በጥሶ ሊጥለው አይደል?" አሉ:: አቶ ምንተስኖት "እኛማ በቁማችን ሞተናል እኮ! ነገ የአካባቢውን ማህበረሰብ ሰብስቤ የፅዳት ዘመቻ ሳላውጅ ከቀረሁ ሞቻለሁ" አሉና እጃቸውን አወናጨፉ::

## 2ኛ ቀን

### አንብቦ መረዳት

**ጥያቄዎቹን በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ፡፡**

1. አቶ ምንተስኖት “በቁማችን ሞተናል!” ሲሉ ምን ማለታቸው ነው?
2. አቶ ምንተስኖት እጃቸውን ያወናጨፉት ለምንድን ነው?

### ቃላት

**ዓረፍተነገር ሥሩ፡፡**

1. ተራባ
2. ተሰበሰበ
3. ተነገረ
4. ተቃጠለ
5. ተከላከለ

### መፃፍ

**በምሳሌው መሠረት ሥሩ፡፡**

| | የግል ንፅህና | የአካባቢ ንፅህና |
|---|---|---|
| ምሳሌ → | ▪ ጥፍር መቁረጥ | ▪ ግቢን ማፅዳት |

## 3ኛ ቀን

### ማዳመጥ

**የንፅህና ጉድለት ጠንቆች**

### ቃላት

**ባዳመጣችሁት መሠረት ባዶ ቦታዎቹን በተስማሚ ቃላት አሟሉ፡፡**

1. የ ________________ በሽታ ከንፅህና ጉድለት ይመጣል፡፡
2. ቤታችንን ካላፀዳን ________________________ ያፈራል፡፡
3. _________________________ የተስቦ በሽታ አስተላላፊ ናት፡፡

## ማጣመር

"አል________ም"ን በመጨመር ቃላትን ፃፉ::

ምሳሌ፡- ታጠበ → አልታጠበም

1. ሠራ    2. ደረቀ    3. ሸተተ    4. ቆፈረ

## ግለንባብ

### በሽታን መከላከል



በንፅህና ጉድለት የሚመጡ በሽታዎችን መከላከል ይቻላል:: ለምሳሌ ፀጉርን፣ ገላንና እጅን በመታጠብ፣ ልብስን በማጠብ የተስቦ በሽታን እንከላከላለን:: ቆሻሻን ሰብስቦ በማቃጠልና በመፀዳጃቤት በመጠቀም የተቅማጥ፣ የዓይን ማዝና የጉንፋን በሽታዎችን መከላከል ይቻላል:: በክረምት የሚያቁሩ ኩሬዎችን በማድረቅ የወባ ትንኝ እንዳትራባ በማድረግ የወባ በሽታን መቀነስ ይቻላል::

## 4ኛ ቀን

## አንብቦ መረዳት

ጥያቄዎቹን በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ::

1. ቆሻሻን ሰብስቦ ማቃጠል ለምን ይጠቅማል?
2. የወባ ትንኝ እንዳትራባ ምን ማድረግ ይገባል?
3. በንፅህና ጉድለት የሚመጡ በሽታዎች ምን ምን ናቸው?

## ማጣመር

በምሳሌው መሠረት ሌሎች ቃላትን መስርቱ፡፡

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ምሳሌ፦ | ሄደ | ሄደች | ሄድን | ሄዳችሁ |
| 1. | አጠበ | | | |
| 2. | ታመመ | | | |
| 3. | ዳነ | | | |


## መፃፍ

ዓረፍተነገር ሥሩ፡፡

1. ያዘ 2. ታመመ 3. ተጣላ 4. ፀዳ

# 16ኛ ሳምንት

## 1ኛ ቀን



### ማዳመጥ

የተዛባ ፍርድ

### ቃላት

በቃላቹሁ ዓረፍተነገር ሥሩ::

ምሳሌ፦ ጅብ → ጅብ ደመሞቃት እንስሳ ነው::

1. አህያ
2. ነብር
3. አንበሳ

### ማጣመር

ፊደላቱንና ቃላቱን አጣምራችሁ አንብቡ::

ምሳሌ፦ የ + ብረት + ድስት → የብረትድስት

1. የ + በጋ + ፀሐይ
2. የ + ዱር + እንስሳ
3. የ + ቤት + እንስሳ
4. የ + ሰውነት + ክፍል
5. የ + ሌሊት + ወፍ

### ግለንባብ

#### የሌሊት ወፎች



የሌሊት ወፎች ከሌሎች ወፎች ይለያሉ:: ሌሎች ወፎች እንቁላል በመጣል ይራባሉ:: የሌሊት ወፎች ግን መሰላቸውን ይወልዳሉ:: በዚህም ምክንያት ከአጥቢ እንስሳት ይመደባሉ:: የሌሊት ወፎች እንደሌሎች ወፎች ክንፍ ቢኖራቸውም ቀን በተቦረቦረ ዛፍ፣ ጨለምለም ባለ ቦታ ወይም በዋሻ ውስጥ ያሳልፋሉ:: ሲተኙም ክንፋቸውን በማጠፍ ራሳቸውን ይዘቀዝቃሉ:: የሌሊት ወፎች የየራሳቸውን ልጆች በድምፃቸው ይለያሉ:: ለስልሳ ቀናት ያህልም ሳያቋርጡ ልጆቻቸውን ይመግባሉ:: የሌሊት ወፎች በአማካይ ለአምስት ዓመታት በህይወት ይኖራሉ::

## 2ኛ ቀን

### አንብቦ መረዳት

**ጥያቄዎቹን በምንባቡ መሠረት በፅሑፍ መልሱ፡፡**

1. የሌሊት ወፍ ልጇን የምትለየው በምንድን ነው?
2. የሌሊት ወፍ ቀን ቀን የት የት ትውላለች?
3. የሌሊት ወፍ በሕይወት የምትኖረው ለምን ያህል ጊዜ ነው?
4. የሌሊት ወፍ ምን ዓይነት እንስሳ ናት?

### ቃላት

**ለቃሎቹ ተቃራኒያቸውን ስጡ፡፡**

ምሳሌ፦ ሌሊት → ቀን

1. ጩኸት
2. ለስላሳ
3. ብርሃን
4. ሙቀት
5. ፍርሃት

### መፃፍ

**ጥያቄዎቹን በፅሁፍ መልሱ፡፡**

1. ደመሞቃት ከሚባሉት እንስሳት ውስጥ አራቱን ፃፉ፡፡
2. እፅዋት በል ከሆኑት እንስሳት ውስጥ ሶስቱን ፃፉ፡፡

## 3ኛ ቀን

### ማዳመጥ

**የተዛባ ፍርድ**

### ቃላት

**ዓረፍተነገር ሥሩ፡፡**

ምሳሌ፦ ቀን → የሌሊት ወፍ ቀን ቀን አትበርም፡፡

1. ብረት
2. ፍየል
3. ላት

## ማጣመር

ቃላቱን አጣምራችሁ በመፃፍ አንብቡ::


ምሳሌ፦ ቤተ+ ክርስቲያን → ቤተክርስቲያን

1. ቤተ + መንግስት → ______ 2. ቤተ + መዘክር ______

## ግለንባብ

### “ጥጋብ ይነዳል ወደረሃብ”

በድሮ ጊዜ ውሻና አህያ ከጌታቸው ቤት ጠፉ:: ሲሄዱ፣ ሲሄዱ ዋሉ:: ለምለም ሳርና ውሃ ያለበት ደረሱ:: ውሻ እጥፍጥፍ ብሎ ተኛ:: አህያ ከሳሩ እስኪበቃት ነጭታ ከውሃው ስትጠጣ በጣም ጠገበች:: ከዚያ በኋላ ውሻን “ልጮህ ነው” አለችው:: ውሻም “ተዪ! ጅብ ይመጣብናል” አላት::



⋆⋆⋆“አህያ የውሻውን ምክር ትሰማለች ብላችሁ ታስባላችሁ?”⋆⋆⋆

እምቢ ብላ “ሃ! ሃ!” ብላ ጮኸች:: ጅብ ሰማ:: ትንሽ ቆይታም ለሁለተኛ ጊዜ ጮኸች:: ጅብ ቀረበ:: ውሻም “እረ ተዪ! የቀድሙ ማሰሚያ፣ ያሁኑ ማቅረቢያ ነው” አላት:: ለሦስተኛ ጊዜ “ሃ! ሃ! ሃ!” ብላ ጮኸች:: ውሻም “በይ የአሁኑ መበያ ነው” አላት:: ወዲያው ጅብ መጣና ሆዷን ዘረገፈው:: ጅብ ቀና ብሎ ሲያይ ውሻው ተጣጥፎ ተኝቷል:: “ደግሞ አንተ ምንድነህ?” አለው:: “ብልት አውጭ ነኝ” አለ-ውሻ:: “በል ና አውጣልኝ!” አለውና ጅብ ተቀመጠ:: ውሻም ልቧን ስልቅጥ አደረገ:: ጅብም “ልቧን ቶሎ በል!” አለው:: “አይ ጌታው፣ ልብማ ቢኖራት መቼ ትበላ ነበር” ብሎ መለሰለት::

## 4ኛ ቀን

### አንብቦ መረዳት

ጥያቄዎቹን በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ፡፡

1. አህያ እንድትጮህ የገፋፋት ምንድን ነው?
2. ውሻስ እጥፍጥፍ ብሎ የተኛው ለምንድን ነው?
3. "ጥጋብ ይነዳል ወደረሃብ" ማለት ምን ማለት ነው?
4. ከምንባቡ ምን ተረዳችሁ?


### ቃላት

የእንስሳቱን ስም ከድምፃቸው ጋር አዛምዱ፡፡

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. ውሻ | ሀ. ሃ፣ ሃ፣ ሃ... |
| 2. ድመት | ለ. አ......ዉ........አ......ዉ... |
| 3. ጅብ | ሐ. ዉ፣ ዉ፣ ዉ... |
| 4. አህያ | መ. ሚያው፣ ሚያው .... |

### መፃፍ

ክቦቹን አሟልታችሁ ፃፉ፡፡



# 17ኛ ሳምንት

## 1ኛ ቀን

### ማዳመጥ



**የህይወት ችሎታ**

### ቃላት

በቃላችሁ ዓረፍተነገር ሥሩ።

1. ድምፅ  2. መርዝ  3. ተናዳፊ  4. ተሳቢ

### ማጣመር


ቃላቱን በማጣመር ፃፏቸው።

ጥቁር → ውሻ
ታማኝ → ውሻ
ጪሂ → ውሻ
ሀይለኛ → ውሻ
ተናካሽ → ውሻ

| ምሳሌ፦ ታማኝ + ውሻ → ታማኝ ውሻ። | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 1. ________ | + | ________ | → | ________ |
| 2. ________ | + | ________ | → | ________ |
| 3. ________ | + | ________ | → | ________ |
| 4. ________ | + | ________ | → | ________ |

### ግለንባብ

## ተሳቢና ተራማጅ እንስሳት



እንስሳት በእግራቸው የሚራመዱ፣ በውሃ ውስጥ የሚዋኙ፣ በምድር ላይ የሚሳቡና በሰማይ ላይ የሚበሩ ተብለው በአራት ዋና ዋና ምድቦች ሊከፈሉ ይችላሉ። ተራማጅ እንስሳት የሚባሉት ከቦታ ቦታ በእግራቸው

ይንቀሳቀሳሉ:: ለምሳሌ እንሽላሊት፣ አዞ፣ እስስት፣ ኤሊና የመሳሰሉት በእግራቸው የሚንቀሳቀሱ ናቸው::

***“ተሳቢ እንስሳት ከቦታ ቦታ የሚንቀሳቀሱት በምናቸው ነው?”***

ተሳቢ እንስሳት የሚባሉት ደግሞ ከቦታ ቦታ የሚንቀሳቀሱት በደረታቸው እየተሳቡ ነው:: ዘንዶ፣ እባብ፣ ትላትልና ቀንድአውጣ በደረታቸው እየተሳቡ የሚንቀሳቀሱ ናቸው::

## 2ኛ ቀን

### አንብቦ መረዳት

**ለጥያቄዎቹ በትዕዛዙ መሠረት በፅሁፍ መልስ ስጡ::**

1. ተሳቢ ከሚባሉት እንስሳት መካከል ሁለቱን ፃፉ::
2. እባብ ከቦታ ቦታ እንዴት ይንቀሳቀሳል?
3. ከተሳቢ ወይም ከተራማጅ እንስሳት አንዱን መርጣችሁ ሳሉና ለመምህራችሁ አሳዩ::

### ቃላት

**በቃላችሁ ዓረፍተነገር ሥሩ::**

ምሳሌ፦ ተሳቢ → ተሳቢ እንስሳ እግር የለውም::

1. ተራማጅ 2. መርዛማ 3. ተናካሽ 4. በራሪ

### መፃፍ

**በምሳሌው መሠረት ሌሎችን ፃፉ::**

ምሳሌ፦ በእግሩ → ይሄዳል ካልን

1. በደረቱ 2. በክንፉ

## 3ኛ ቀን

### ማዳመጥ

## የህይወት ችሎታ

### ቃላት

በምሳሌው መሠረት ሌሎችን አሟሉ::

ምሳሌ፦ አንበሳ በክርኑ ይደቁሳል::

1. አዞ በጥርሱ 2. ጃርት በእሾኋ 3. አጋዘን በቀንዱ

### ማጣመር

ፊደላቱን ከቃላቱ ጋር አጣምራችሁ ፃፉና አንብቡ::

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ስለ | እንደ | በ | ከ | ለ |

ምሳሌ፦ ስለ + መጣ → ስለመጣ

1. _ +እግር
2. _ + ክረምት
3. _ + በጋ
4. _ + አባቱ
5. _ + ጓደኛ

### ግለንባብ

## ታማኝ ውሻ



አንድ ቀን አቶ ብርሃኑ ውሻውን አስከትሎ ወደ እንጦጦ ጫካ ሄደ:: ጫካውም በተለያዩ እፅዋት የተሞላ ነው:: በጉች ችግኞቹን ሲበሉ ተመለከተ:: ከውሻው ጋር እያባረራቸው ወደ ዛፎቹ መሀል ገባ::

***"አቶ ብርሃኑና ውሻው ወደ ዛፎቹ ሲገቡ ምን የሚያጋጥማቸው ይመስላችኋል?"***

በድንገት አንድ የነጋበት ጅብ ከአቶ ብርሃኑ ጋር ተፋጠጠ። ውሻውም በጅቡ ላይ ተከመረበት። ጅቡ አቶ ብርሃኑን ትቶ ወደውሻው ዞረ። በዚህ ጊዜ አቶ ብርሃኑ "ድረሱልኝ ፤ ኡ! ኡ! ኡ!" እያለ ጮኸ። የመናፈሻው ዘበኞችም ጩኸት ወደሰሙበት መሳሪያቸውን ይዘው እየሮጡ ሄዱ። ሲደርሱ ጅቡ ግራ ተጋብቶ ሲቅበዘበዝ አገኙት። ዘበኞቹም በያዙት መሳሪያ ተኩሰው ገደሉት።

## 4ኛ ቀን

### አንብቦ መረዳት

በምንባቡ መሠረት ጥያቄዎችን በቃላችሁ መልሱ።

1. አቶ ብርሃኑ ውሻውን አስከትሎ የሄደው ወደየት ነው?
2. ከአቶ ብርሃኑ ጋር የተፋጠጠው ምንድን ነው?
3. ውሻውስ ምን አደረገ?
4. ተረቱ ምን ያስተምራችኋል?

### ቃላት

እግር ያላቸውና እግር የሌላቸው እንስሳትን መድባችሁ ፃፉ።

| እግር ያላቸው | እግር የሌላቸው |
| --- | --- |
| ምሳሌ፦ አዞ | ምሳሌ፦ እባብ |

### መፃፍ

ዓረፍተነገር ስሩ።

ምሳሌ፦ በእግር → በእግር መጓዝ ጤናማ ያደርጋል።

1. ስለመጣ
2. ለክረምት
3. በበጋ
4. እንደኋደኛው
5. ከአባቴ ጋር